


يهدى
والأيام
شهر رمضان الذي أنزل فيه القرآن
صيام رمضان
فضائله . آدابه . أحكامه . قيامه
የረመዳን ፆም
إعداد
محمد بن جميل زينو
المدرس في دار الحديث الخيرية بمكة المكرمة
الطبعة السابعة



አዘጋጅ ሼኽ መሐመድ ቢን ጀሚል ዘይኑ
በመከተል ሙከረማ የዳረል ሐዲስ ኸይሪያ መምህር
ትርጉም ሰይፈዲን ሐበሻ
ከጅዳ የኢትዮጵያዊያኖች የዳዕዋ ማዕከል
1427 ዓመተ ሂጅራ

ማውጫ

ተ.ቁ.	ርዕስ	ገፅ. ቁ.
1	መቅደም	5
2	ስለ ፆም ከቁርአን አንቀፅ	6
3	ከቁርአኑ አንቀፅ የሚገኙ ጥቅሞች	7
4	የረመዳን ፆም ከኢስላም መሠረቶች አንዱ ነው	8
5	የረመዳን ፆም ብያኔ	9
6	የረመዳን ወርና የፆም ጥቅሞች	10
7	በረመዳን መደረግ የሚገባቸው	12
8	የፆም ሱናውና ሥርዓቱ	13
9	ከፆም ጥቅሞች በመጠኑ	14
10	ፆም የሚከለከሉባቸው ቀኖች	16
11	ፆም የሚጠሉባቸው ቀኖች	17
12	በረመዳን ማፍጠር የሚፈቀድላቸው	18
13	ፆም የሚያፈርሱ ነገሮች	18
14	ፆም የማያፈርሱ ነገሮች	19
15	የውዴታ ፆሞችና ጥቅማቸው	21
14	ጥብቅ ማሳሰብያ	23
15	የረመዳን ሌሊት ሰላት (ቂያም)	23
16	ለይለተል ቀድርና ትሩፋቱ	24
17	ኢዕቲካፍ	25
18	ዘካተል ፊጥር	27
19	የሁለቱ ዒዶች ሰላት	28
20	በዒድ ቀን የሚታዩ ፈጠራዎች	30
21	ተቀባይነት ያላቸው ዱዓዎች	31
22	የፈውስ ዱዓ	32
23	የምርጫ ዱዓ	33
24	የመንገደኛና የተሳፋሪ ዱዓ	34

بسم الله الرحمن الرحيم

إن الحمد لله نحمده، ونستعينه، ونستغفره، ونعوذ بالله من شرور أنفسنا وسيئات أعمالنا، من يهده الله؛ فلا مضل له، ومن يضلل؛ فلا هادي له. وأشهد أن لا إله إلا الله وحده لا شريك له، وأشهد أن محمداً عبده ورسوله صلى الله عليه وعلـــى آلـــه وصحبه وسلم.

ምስጋና ለአላህ ስለተገባው እናመሰግነዋለን በሱም እንረዳለን ምህረትም እንከጅላለን ከነፍሶቻችን ሸሮችና ከወንጀል ሥራዎቻችን በአላህ እንጠበቃለን አላህ ቀጥተኛውን መንገድ የመራው ማንም አያጣመውም የተጣመመን ደግሞ ከአላህ በስተቀር ማንም አይመራውም:: ከአላህ በስተቀር በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባው አምላክ የለም አላህ አንድ ነው ሸርክም የለውም ነብዩ መሐመድም የአላህ አገልጋይ እና መልዕክተኛ መሆናቸውን እንመሰክራለን ሰላምና ሰላት በአላህ መልዕክተኛ በቤተሰባቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን ::

መቅደም

የረመዳን ፆም ማለት ከአምስቱ የኢስላም መሠረቶች አንዱ ሲሆን በዚህም ፆም ወቅት በሙስሊሞች ላይ ፍፁምነት ኢማንና ታማኝነት በጣም ጎልቶ ይታይባቸዋል ። ፆመኛ ከመጠጥ ፣ ከምግብና ፆምን ከሚያገድፉ ነገሮች ሁሉ በሚታቀብበት ጊዜ አላህ እንደሚቆጣጠረውና እንደሚያየው ፍፁም እርግጠኛ ይሆናል።

በዚህች መፅሐፍ ላይ ያቀረብኩት ስለፆም ጥቅም ፣ ሥነ - ሥርዓት ፣ ብያኔ ፣ ስለሚያስፈጥሩ ነገሮች ፣ ስለሌሊት ሰላት ፣ ስለ ለይለቱል ቀድርና ጥቅሙ ፣ ስለ ኢዕቲካፍ ፣ ስለዘካተል ፊጥር ፣ ስለዒዶች ሰላትና ስለሌሎችም አስፈላጊ ነጥቦች ተጠቅሰዋል።

መፅሐፍዋ ለሙስሊሞች ጠቃሚ እንድትሆንና ሥራውም ፍፁም ለሊላህ እንዲሆን አላህን እጠይቀዋለሁ ።

መሐመድ ቢን ዘይኑ -- (በአረብኛ የመፅሐፉ አዘጋጅ)

ተርጊሚው -- ለዚሕች መፅሐፍም ሆነ ለሌሎች የትርጉም ሥራዎች ከጎኔ በመቆም ለሥራው ጥራት ከፍተኛ አስተዋፆ ለሚያደርጉት በጅዳ ለሚገኙት የኢትዮጵያዊያኖች የዳዕዋና የትምህርት ማዕከል የኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ለመልካም ሥራቸው ምንዳ እንዲያገኙበት አላህን እለምነዋለሁ።

ሰይፈዲን ሐበሻ

ስለ ፆም ከቁርአን አንቀፅ

قال تعالى: ﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ١٨٣ أَيَّامٗا مَّعۡدُودَٰتٖۚ فَمَن كَانَ مِنكُم مَّرِيضًا أَوۡ عَلَىٰ سَفَرٖ فَعِدَّةٞ مِّنۡ أَيَّامٍ أُخَرَۚ وَعَلَى ٱلَّذِينَ يُطِيقُونَهُۥ فِدۡيَةٞ طَعَامُ مِسۡكِينٖۖ فَمَن تَطَوَّعَ خَيۡرٗا فَهُوَ خَيۡرٞ لَّهُۥۚ وَأَن تَصُومُواْ خَيۡرٞ لَّكُمۡۖ إِن كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ١٨٤ شَهۡرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلۡقُرۡءَانُ هُدٗى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡهُدَىٰ وَٱلۡفُرۡقَانِۚ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُۖ وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوۡ عَلَىٰ سَفَرٖ فَعِدَّةٞ مِّنۡ أَيَّامٍ أُخَرَۗ يُرِيدُ ٱللَّهُ بِكُمُ ٱلۡيُسۡرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ ٱلۡعُسۡرَ وَلِتُكۡمِلُواْ ٱلۡعِدَّةَ وَلِتُكَبِّرُواْ ٱللَّهَ عَلَىٰ مَا هَدَىٰكُمۡ وَلَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ١٨٥ ﴾

ትርጉሙ ((እናንተ ያመናችሁ ሆይ ፆም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩ (ህዝቦች) ላይ እንደተደነገገ በናንተም ላይ ተደነገገ ልትጠነቀቁ ይከጀላል እና የተወሰኑ ቀኖች (ፁሙ) ከናንተ ውስጥ በሽተኛ ወይንም በጉዞ ላይ የሆነ ሰው ከሌሎች ቀኖች የተወሰነውን መፆም አለበት በነዛም ፆምን በማይችሉት ላይ ቤዛ ድሃን ማብላት አለባቸው (ቤዛን በመጨመር) መልካምንም ሥራ የፈቀደ ሰው እርሱ

(ፈቅዶ መጨመሩ) ለርሱ በላጭ ነው መፆማችሁም ለናንተ የበለጠ ነው የምታውቁ ብትሆኑ (ትመርጡታላችሁ) ፣ (እንድትፆሙ የተፃፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (ውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀፆች) ሲሆን ቁርአን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው ከናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይፁመው በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነ ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መፆም አለበት አላህ በናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል በናንተም ችግሩን አይሻም ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህን ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህን ደነገገላችሁ) ::)) በቀራ // 183-185 //

ከቁርአኑ አንቀፅ የሚገኙ ጥቅሞች

1. ፆም በዱንያም ሆነ በአኼራ ልዩ ጥቅሞች ስላሉት አላህ በቀድሞዎቹ ህዝቦች ላይ ግዴታ እንዳደረገው ሁሉ በሙስሊሞችም ላይ ግዴታ አደረገው::
2. ፆም ለአላህ ያለንን ፍራቻ (ተቅዋ) ከፍ ያደርጋል::
3. የረመዳን ፆም ቀኖቹ የተወሰኑ ናቸው ከሰላሳ ቀኖችም አይበልጡም::
4. ሕመምተኛ እና በጉዞ ላይ ያሉ ሙስሊሞች በረመዳን ፆም ማፍጠር ሲችሉ ቀኟ ማውጣት ግን ግዴታቸው ነው::

5. መጀመርያ በረመዳን የፈለገ አፍጥሮ ካሳውን (ፊዲያ) መክፈል ምርጫ ነበረው ከላይ በተነበበው የቁርአን አንቀፅ ይህ ምርጫ ተሽሮ መፆም ብቻ ግዴታ ሆነ።
6. ቁርአን የወረደው በረመዳን ወር ነው ፡ በዚህ አጋጣሚ ቁርአን ወረደ ሲባል ከሰማይ ወደ መሬት መሆኑን ያመለክታል ይኸውም አላህ ካለበት አርሽ ወደ ምድር ወረደ ማለት ነው ይህንኑ አቂም ሌሎች የቁርአን አንቀፆችና ሐዲሶች ያረጋግጡታል።
7. ለአካለ መጠን የደረሱ ሙስሊሞች ላይ ፆም ግዴታ መሆኑን ያመለክታል።
8. የአላህ ሕግ ገርና ከማስጨነቅ የራቀ መሆኑን አንቀፁ ይመሰክራል።
9. ሙስሊሞች የዒድ ቀን አላህን በማተለቅ ፣ ተክቢራ በማለት ፀጋውን ማመስገን እንደሚገባቸው ይጠቁማል።

የረመዳን ፆም ከኢስላም መሠረቶች አንዱ ነው

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ኢስላም በአምስት ተገነባ አሉ) ይኸውም ፡-

1 ላኢላሃ ኢለሏህ በማለት የአላህን አንድነት መመስከር፡- በተጨማሪ በሐቅ የሚገዙት አምላክ ከአላህ በስተቀር የለም ማለት ሲሆን መሐመደን ረሱሉሏህ ብሎ መመስከር ማለት አላህ ነብዩ መሐመድን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የአላህ ዲን ኢስላምን እንዲያስተላልፉ መላካቸውን ማመንና ትዕዛዛቸውን መፈፀም ነው።

2 ሰላትን በወቅቱ ሥርዓቱንና ደንቡን ጠብቆ በእርጋታና በተመስጦ (በኹሹዕ) መስገድ::

3 ዘካት መስጠት :- ይኸውም ሙስሊም ከሰማንያ አምስት ግራም በላይ የሚመዝን ወርቅ ካለው ወይንም የሰማንያ አምስት ግራም ወርቅ ግምት ያህል ገንዘብ ካለው ሁለት ነጥብ አምስት ከመቶ (2 . 5 ፐርሰንት) ለምስኪን መስጠት ሲሆን ከወርቅና ከጥሬ ገንዘብ ውጪ በሆነ ንብረት ላይ እራሱን የቻለ የአከፋፈል ዝርዝር አለው (ለጥሬ ገንዘብ ለወርቅም ሆነ ለሌላ ንብረት ዘካ ማውጣት ግዴታ የሚሆነው አንድ ዓመት ሲሞላው ነው::)

4 ሐጅ ማድረግ :- የመጂጊኛና የቀለብ ገንዘብ ኖሮት ለቤተሰቡ በቂ ወጪ ያስቀመጠና ዕዳ የሌለበት ጤነኛ ሙስሊም ላይ በሕይወት ዘመኑ አንድ ጊዜ ሐጅ ማድረግ ግዴታ ነው::

5 የረመዳንን ወር መፆም :- ፈጅር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ከምግብ ፣ ከመጠጥ ፣ ከግብረ ሥጋ ግንኙነትና ከሌሎችም ፆምን ከሚያበላሹ ነገሮች ተቆጥቦ መፆም ለአካለ መጠን በደረሱ ሙስሊሞች ላይ ሁሉ ግዴታ ነው::

<u>የረመዳን ፆም ብያኔ</u>

1 ፆም ማለት አላህን ለመገዛት አስቦ ፈጅር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ከምግብ ፣ ከመጠጥ ፣ ከግብረሥጋ ግንኙነትና ፆም ከሚያፈርሱ ነገሮች መቆጠብ ማለት ነው::

2 የረመዳን ፆም ብያኔ :- ፆም ሙስሊም የሆነ ፣ ለአካለ መጠን የደረሰ ፣ ጤነኛ የሆነ ፣ መንገደኛ ያልሆነ ላይ ሁሉ ግዴታ ነው : ሴቶችም ሲፆሙ ከወር አበባና ከወሊድ ደም የጠሩ መሆን አለባቸው::

3 የረመዳን ወር መግባቱ የሚታወቀው አዲስ ጨረቃ በማየት ወይንም የሻዕባንን ወር ሰላሳ ቀን በመሙላት ሲሆን ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ጨረቃን አይታችሁ ፁሙ አይታችሁ አፍጥሩ (ለማየት)

ከተሸፈነባችሁ የሻዕባንን ወር ሰላሳ ቀን ሙሉት) ብለዋል::

4 የኒያ ብያኔ :- ለረመዳን ፆም መነየት ግዴታ ሲሆን ፆመኛ በልቡ ከነየተ በቂ ነው ድምፅን አሰምቶ መነየት ለፆምም ሆነ ለሰላት ምን መረጃ የለውም : ለምሳሌ ከፈጅር በፊት ሰሑር የበላ ነየተ ማለት ነው : ሌላው ለሊላህ ብሎ ለመፆም ከምግብ ከመጠጥና ከሚያፈጥሩ ነገሮች የተቆጠበ ነየተ ማለት ነው::

የረመዳን ወርና የፆም ጥቅሞች

1 አላህ በቁርአኑ (... ቁርአን የወረደበት የረመዳን ወር ነው ...) ብሎዋል :: አል በቀራህ 185

2 አላህ በቁርአኑ :-

قال تعالى: ﴿ إِنَّآ أَنزَلۡنَٰهُ فِي لَيۡلَةِ ٱلۡقَدۡرِ ۝ ﴾

ትርጉም ((እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት (በተከበረችው ሌሊት በረመዳን) አወረድነው))

አል ቀድር - 1

3 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ረመዳን ሲገባ የሰማይ በሮች ይከፈታሉ የጀሐነም በሮች ይዘጋሉ ሸይጣኖች ይታሰራሉ) ብለዋል::

በሌላ ሐዲስ (ረመዳን ሲመጣ የጀነት በሮች ይከፈታሉ) በሌላ ሐዲስ (የእዝነት በሮች ይከፈታሉ) ብለዋል::

4 ተርሙዚ ባወሩት ሐዲስ (ረመዳን ሲገባ ተጣሪው ይጣራል :- (መልካም ፈላጊ ሆይ ና ፤ ተሰብሰብ ጠጋ በል : ሸር ፈላጊ ሆይ ተመለስ (ሸርህን አቁም) ይላል:: ረመዳን እስኪያልቅ ድረስ በየቀኑ አላህ ከእሳት ነፃ የሚያወጣቸው ባሮች አሉት::)

5 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አላህ እንዲህ ብሏል አሉ (የአፃም ዘር (መልካም) ሥራው በሙሉ ይደራረብለታል አንድ ሐሰና ከሰባት እስከ ሰባት መቶ ወይንም አላህ እስከፈለገው ድረስ እጥፍ ይሆንለታል: ፆም ብቻ ሲቀር ፆም የኔ ነው ምንዳውን እኔ ነኝ የምከፍለው ፆመኛ ለኔ ብሎ ከምግብና ከመጠጥ

ታግዷልና: ያመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት አንደኛው ደስታ ሲያፈጥር ሲሆን ሁለተኛው ደስታ ጌታውን ሲገናኝ ነው ፣ የያመኛ ሰው የአፉ ጠረን አላህ ዘንድ ከምስክ ሽቶ የበለጠ ያማረ ሽታ አለው ::)

ብለዋል ቡኻሪና ሙስሊም

6 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ጀነት ውስጥ ረያን የሚባል ያመኛ የሚገባበት በር አለ በዚህም በር የቂያም ቀን ያመኞች ከገቡበት በኋላ በሩ ይዘጋል ካለነሱም በስተቀር ማንም አይገባበትም) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም

7 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የረመዳንን ያም የአላህ ትዕዛዝ መሆኑን አምኖበት (በኢማን) ምንዳ አገኝበታለሁ ብሎ (በኢሕቲሳብ) የያመ ሰው ያለፈው ወንጀሉ በሙሉ ይማርለታል) ብለዋል::

8 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (በአምስቱ ሰላቶች መካከል ከጁምዓ እስከ ጁምዓ ፣ ከረመዳን እስከሚቀጥለው ረመዳን ባሉት ጊዚያቶች ከትላልቅ ወንጀሎች የራቀ ሌሎች ይማራሉ (ይታበሳሉ) ብለዋል :: ሙስሊም እንደዘገቡት

9 አቢ ኡማማ እንዳሉት ወደ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ቀርቤ ጀነት የሚያስገባኝ ሥራ ይምሩኝ አልኳቸው (በያም በርታ ከሱ የሚስተካከል የለምና አሉኝ) ለሁለተኛ ጊዜ ስጠየቃቸው (በያም በርታ) አሉኝ ይላሉ:: አህመድ እንደዘገቡት

10 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (አንድ የአላህ ባርያ በአላህ መንገድ ላይ ሆኖ ከያመ ያቺን የያመበትን ቀን የሰባ አመት (ጉዞ) ርቀት ያህል ፊቱን ከእሳት ያርቅለታል) ብለዋል:: ሙስሊም እንደዘገቡት

11 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ያምና ቁርአን የቂያም ቀን ለአላህ ባርያ ዋስ ይሆናሉ ፣ ይኸውም ያም ይላል :-ጌታዬ እኔ በቀን ከምግብና ከስሜቱ ከለከልኩት ዋስ ሆኛለሁና ዋስትናዬን ተቀበለኝ ይላል) አሉ:: አህመድና ሌሎችም እንደዘገቡት

በረመዳን መደረግ የሚገባቸው

ሙስሊም ወንድሜ ሆይ ዋና ማወቅ የሚገባህ ነገር አላህ እሱን ብቻ እንድናመልክ ብሎ በሙስሊሞች ላይ ያምን ግዴታ አደረገብን ታድያ ይህ ያምህ እንዲጠቅምህና የተሟላ እንዲሆን የሚከተሉትን አድርግ፡-

1. ሰላትን አስተካክሎ መስገድ ፡- ሰላት የዲን ምሰሶ ስለሆነ ሰላት መተው ያከፍራል።
2. ለረመዳን ያም ትኩረት መስጠት፡- ይኸውም ልጆችህ አቅማቸው ሲችል እንዲያሙ አለማምዳቸው ያለአንዳች ምክንያትም እንዳያፈጥሩ አስጠንቅቃቸው ። ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በተኙበት (በህልማቸው) እንዳዩት (ሰዎች በአንገቶቻቸው ተንጠልጥለው ጉንጮቻቸው ተቀዶ ደም ይፈስባቸዋል እነዚህ እነማን ናቸው? ብለው ሲጠይቁ እነዚህማ ያም ሳይፈታ (ከፉጡር ወቅት በፊት) የሚያፈጥሩ ናቸው ተባሉ። ሐከም ትክክል ብለው ዘሃቢ የተስማሙበት ሐዲስ
   አንዲትን ቀን አውቆ የረመዳንን ያም ያለምክንያት ያፈጠረ ተውበት አድርጎ ቀዷ ማውጣት አለበት።
3. በማንኛውም አጋጣሚ በረመዳን ያም ካፈጠርክ በሰዎች ፊትለፊት አታፍጥር ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ሁሉም ዑመቴ ይማራሉ ወንጀላቸውን ግልፅ ያወጡ ብቻ ሲቀሩ) ብለዋል። ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት
   .
   ሌላው ዒድ ማለት ደስታ ማለት ስለሆነ የረመዳንን ያም ያልያመ ሰው የዒድ ደስታ የለውም ምክንያቱም የረመዳንን የያም ዒባዳ በትክክል የፈፀመ አላህ ለእንደዚህ አይነት ዒባዳ ስላበቃው ሊደሰት ይገባዋል የረመዳንን ያም በትክክል ያልያመ በዒድ ቀን ደስታ ሳይሆን ማዘን ነው የሚገባው።
4. በረመዳን ያም ፀባየ ሸጋ መሆን ያስፈልጋል በተለይ ዲንን መስደብ ኩፍር ነውና መጠንቀቅ ያስፈልጋል ፡ ከሰዎች ጋር ያለህ አቀራረብ የተጠላ መሆን የለበትም ፡ ያምህ ፀባይህን የሚያስተካክል መሪ መሆን አለበት እንጂ

በያምህ ምክንያት እየተበሳጨህ ፀባይህ የተበላሸ መሆን የለበትም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (አንዳችሁ በያማችሁ ቀን እንዳይረክስ (ፀያፍ ቃል እንዳይናገር) እንዳይጮህም አንዱ ቢጣላው ወይንም ቢሰድበው እኔ ያመኛ ነኝ ይበል) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት

5. ምላስን መጠበቅ :- በያም ሰውን ከማማትና ከማሳበቅ የመሳሰሉትን ድርጊቶች መጠንቀቅ ግዴታ ነው ይኸውም (ሀ) .ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (መጥፎ ቃልንና መጥፎ ስራን ሳይተው (የያመ) ምግብንና መጠጥን ብቻ ስለተወ ለአላህ ምንም ጉዳዩ አይደለም (ምንዳም አያገኝበትም) ብለዋል:: ቡኻሪ.እንደዘገቡት .
(ለ) (ስንት ፂሚ ከያሙ ከጥማት በስተቀር ምንም አያተርፍም) ብለዋል:: ዳረሚ

6. ስለያም ማብራሪያ የያዙ መልዕክቶችን ማንበብ ብያኔዎችንም (አሕካም) ሆነ ሌሎችን መመሪያዎች ማወቅ ግዴታ ነው : ለምሳሌ በመርሳት መብላትና መጠጣት ያምን አያበላሽም ፣ ጀናባ ሆኖ የነጋበት ያምን ከመያዝ የሚያግደው ነገር የለም ለጧሃራና ለሰላት ሲሆን ግን መታጠብ ግዴታው ነው::

የያም ሱናውና ሥርዓቱ

1. ሰሑር ኢፍጣርና ዱዓን በተመለከተ ረሱል (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) .
(ሀ) (ሰሑር ብሉ ሰሑር ላይ በረካ አለ) ብለዋል::
(ለ) (ሰዎች ቶሎ በማፍጠር እስከተቻኮሉ ድረስ ከመልካም አይርቁም) ብለዋል:: .
(ሐ) ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የመግሪብን) ሰላት ከመስገዳቸው በፊት በእሸት ተምር ያፈጥሩ ነበር እሸት ካልተገኘ እሸት ባልሆነ በሳል ተምር ያፈጥሩ ነበር በሳል ከጠፋ ውሃ በመጎንጨት ያፈጥሩ ነበር) ተርሚዚና ሌሎችም ያወሩት
(መ) የሦስት ሰዎች ዳዕዋ ተመላሽነት የለውም (እነሱም) ያመኛ እስኪያፈጥር ድረስ ፣ የማያዳላ መሪ ፣ የተበደለ ሰው ዱዓ ናቸው:: ተርሙዚና ሌሎችም ያወሩት

(ሠ) ረሱል (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ካፈጠሩ በኋላ (ዘሃበ ደመኡ ወብተለተል ዑሩቅ ወሰበተል አጅር ኢንሻ አላህ) ይሉ ነበር ። ትርጉም (ጥም ተወገደ የደም ሥር ተብላላ የአላህ ፍላጎት ከሆነ ምንዳውም ፀደቀ) ማለት ነው።

2. በረመዳን አላህን በብዙ ማውሳት ፣ ቁርአን መቅራትና መስማት ትርጉሙን አውቆ በተግባር ማዋል ፣ ጠቃሚ የሆኑ የዲን ትምህርቶችን ለመከታተል መስጊድ መሄድ የተወደዱ ሥራዎች ናቸው።
3. እርዳታ ለሚፈልግ ዘመድና ለቸገረው ሰደቃ ማብዛት ፣ ቤተዘመድ መጠየቅ ፣ ፀበኛን መታረቅ ፣ በጣም ትጉህና ለጋሽ መሆን ተገቢ ነው። ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በመልካም ነገር ከሰዎች ሁሉ የበለጡ ትጉህ ነበሩ ረመዳን ሲገባ የበለጠ ይተጉ ነበር።
4. ምግብና መጠጥ እያባከንክ አታፍጥር ያምህን ዋጋ ቢስ አድርገህ ጤናህን ትጎዳለህና፡ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (በኒ አደም የሆዱን ከረጢት ሲሞላ ሸሩ ነው) አሉ ።
5. ሙዚቃና ዘፈን የሰይጣን መዛሚር (መሣሪያ) ስለሆነ አታዳምጥ።
6. ወደ ፊልም ቤት ያለመሄድ ፣ በቴሌቭዢን የሚተላለፉ ጣቢያዎች አብዛኛዎቹ ፀባየ ብልሹ የሚያደርጉና ከያም ጋር ስለሚቃረኑ መራቅ ያስፈልጋል።
7. ማታማታ በጣም ያለማምሸት ምክንያቱም ለሰሑርና ለፈጅር ሰላት ለመነሳት ያዳግታልና በተጨማሪ በጠዋት በጊዜ ተነስቶ ወደ ሥራ ለመሰማርት እንዲመች ያለማምሸት የተመረጠ ነው ። ረሱል (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) (አላህ ሆይ ከሕዝቦቼ አበካሪዎችን (በጊዜ ለሚገኙ) ባርካቸው) በማለት ዱዓ አድገዋል ስለዚህ ጠዋት በጊዜ መነሳት በረካ አለው።

ከያም ጥቅሞች በመጠኑ

ሙስሊም ወንድሜ ሆይ አላህ ያምን ግዴታ ሲያደርግብን በያም ዙርያ ብዙ ጥቅሞች እንዳሉ ማወቅ ይገባሃል፦

1. ስለ ፆም ጥቅም አላህ በቁርአኑ ሲያወሳ በፆም ሰበብ ከፍተኛ አላህን የመፍራት (ተቅዋ) ደረጃ ይደረሳል።
2. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ፆም ጋሻ ነው) ብለዋል። ቡኻሪና ሙስሊም (ጋሻነቱም ከወንጀል ፣ ከመጥፎ ሥራ ፣ ከእሳት ከመሳሰሉት ሸሮች ይከላከላል)።
3. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ፆመኛን ያስፈጠረ ሰው ከፆመኛው ምንም ሳይቀነስ የፆመኛውን ያህል ምንዳ ያገኛል) ብለዋል። ተርሙዚ እንደዘገቡት
4. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (በረመዳን የተደረገ ዑምራ ምንዳው እንደ ሐጅ ምንዳ ነው) ብለዋል። ቡኻሪና ሙስሊም
5. ሲጋራ የሚያጨስ ሙስሊም በረመዳን ለመተው ጥሩ አጋጣሚ ስለሆነ አጫስ በቀን ማጨስ እንደተወው ሁሉ በማታም በመተው ይህንን ዕድል ሊጠቀምበት ይገባል። እንደሚታወቀው ሲጋራ ማጨስ ለካንሰርና ለሌሎችም በሽታዎች ሰበብ ስለሚሆን በኢስላም ሸሪዓ ጎጂ ነገር በጣም የተጠላና ሐራም ነው።
6. በፆም ሰበብ ያለማቂረጥ የሚሰሩ ጨጊራና ምግብ የሚያስተላልፉ አካሎች እረፍት ስለሚያገኙ ሰውነትን በማጠንከር ለጤንነት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው።
7. ፆም ነፍስን በማረጋጋት ወደ በጎ ሥራ ከመገፋፋትም በተጨማሪ ትዕግስትን ፣ ፍፁምነትን ፣ ሥርዓትን ፣ መንፈሰ ጠንካራነትንና ለአላህ መታዘዝን ያጎናፅፋል ።
8. ፆመኛ ከሙስሊም ወንድሞቹ ጋር አብሮ እየፆመ አብሮ ሲያፈጥር ኢስላም ሰብሳቢና አንድነትን አምጪ መሆኑን ይረዳል።
9. ፆመኛ እርሃብ ሲሰማው የቸገረውንና የራባቸውን ወንድሞቹን ስለሚያስታውስ ከምንግዜውም በበለጠ ለተቸገሩና ለምስኪኖች ይመፀውታል (ሰደቃ ያበዛል)።
10. ፆመኛ የአላህን ትዕዛዝ ለማክበርና ውዴታውን ለማግኘት ብሎ ሐላል የሆነውን ምግብና መጠጥ በሚተውበት ጊዜ ሐራም የሆኑትን ነገሮች ለመተው በይበልጥ ይነሳሳል።
11. ፆመኛ ቀኑን ሙሉ ከሚያስፈጥሩ ነገሮች ተከልክሎ ሲውል አላህ እንደሚቆጣጠረው ስለሚያውቅ በጣም

ጥንቁቅ ይሆናል ይህንንም ጥንቁቅነትን ይላመደውና ከሰዎችም ጋር ያለው ግንኙነት ታማኝነትን የተላበሰ ይሆናል በተጨማሪም በግልፅም ሆነ በስውር ለአላህ ያለው ፍራቻ ይጨምራል።

ፆም የሚከለከሉባቸው ቀኖች

1. ሁለቱን የዒድ ቀኖች ማለትም ዒደል ፊጥር እና ዒደል አድሐ መፆም የተከለከለ ነው ዑመር ኢብኑ ኸጣብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዳሉት (እነዚህ ሁለት ቀኖች ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳይፆምባቸው በማለት ከልክለዋል ቀኖቹም አንደኛው ፆማቹሁን የምታፈጥሩበት ቀን ሲሆን ሁለተኛው እርዳችሁን የምትበሉበት ቀን ነው) አሉ።
2. ሴቶች በወር አበባና በወሊድ ደም ጊዜ መፆም አይፈቀድላቸውም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሴቶች በዲናቸው እንደጎደለባቸው ሲያብራሩ (ሴት በወር አበባ ጊዜ መፆምም ሆነ መስገድ አትችልም አይደለም እንዴ ? ታድያ እነዚህ ናቸው እኮ በዲኗ ላይ ያጎደሉባት) አሉ። ቡኻሪ እንደዘገበው
3. ሳያፈጥሩ ሁለት ቀኖች (48 ሰዓት) አከታትሎ መፆም ክልል ሲሆን ይህም ኢቲፓም (ዊሷል) በመባል ይታወቃል ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ዊሷልን ተጠንቀቁ) ብለዋል። ቡኻሪና ሙስሊም .
በሌላው ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ሁለት ቀን ቀጣጥላችሁ አትፁሙ ከናንተ ውስጥ ቀጣጥሎ መፆም ያማረው እስከ ሰሑር ድረስ ብቻ ይቀጥል) ብለዋል ::
4. የጥርጣሬ ቀን መፆም ክልክል ነው :- ይህ የጥርጣሬ ቀን የሚባለው የሻዕባን ሰላሳኛው ቀን ሲሆን የሻዕባን ወር ሃያ ዘጠኝ መሆኑን በጨረቃ እይታ ሳይረጋገጥ ሻዕባን ሰላሳ ምናልባት ረመዳን አንድ ይሆናል በማለት በጥርጣሬ መፆም ክልክል ነው። ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ከረመዳን በፊት አንድ ቀን ወይንም ሁለት ቀን አስቀድማችሁ አትፁሙ አንድ ሰው ያስለመደው ፆም ካለ

ግን ይፁም) ብለዋል:: ሙስሊም እንደዘገቡት .
(ያስለመደው ፆም ማለት እንደ የሰኞና የሐሙስ ፆሞች አይነት ናቸው::

ፆም የሚጠሉባቸው ቀኖች

1. ሐጅ ያደረገ ሰው ዓረፋ ላይ ሲቆም መፆም ክልክል ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ግመል ላይ ሆነው ዓረፋ በቆሙበት ኡሙ ፉዶል የላከችውን ወተት ጠጥተዋል) ሙስሊም እንደዘገበው (ይህ የሚያመለክተው ሐጅ የሚያደርግ ሰው የውቁፍ ቀን መፆም እንደሌለበት ነው::)
2. የጁምዓን ቀን ለብቻው ነጥሎ መፆም ክልክል ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የጁምዓን ቀን ከፊትለፊቱ ወይንም ከበስተኋላ አንድ ቀን ሳታስከትሉ ለብቻው እንዳትፆሙ) ብለዋል::
3. የቅዳሜን ቀን ለብቻው መፆም ክልክል ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ፈርድ ካልሆነ በስተቀር የቅዳሜን ቀን ለብቻው እንዳትፆሙ አንዳችሁ የሚያፈጥርበት አጥቶ እንጨትና የዛፍ ልጥ ብቻ ቢያገኝ እንኳን በነሱም ቢሆን ያፍጥር) ብለዋል:: አህመድና ሌሎችም እንዳወሩት
4. አመቱን በሙሉ መፆም ክልክል ነው:: ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ዘወትር (በየቀኑ ያለማቋረጥ) የሚፆም ፆም የለውም) ብለዋል:: ሰሒሕ ነሣኢ
5. ሴት ባሏ አጠገቧ እያለ ያለፈቃዱ በስተቀር መፆም አይፈቀድላትም:: ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ባሏ አጠገቧ ያለ ሴት በባሏ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር እንዳትፆም ረመዳን ብቻ ሲቀር) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም
6. ሦስቱን አያመተሸሪቅ ቀኖች አይፆምባቸውም አያመተሸሪቅ የሚባሉት ዙልሂጃ 11 -- 12 -- 13 ናቸው:: ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (አያመተሸሪቅ የምግብና የመጠጥ እንዲሁም አላህ የሚወሳባቸው ቀኖች ናቸው) ብለዋል:: ሙስሊም

በረመዳን ማፍጠር የሚፈቀድላቸው

1. ሕመምተኛና መንገደኛ በረመዳን ማፍጠር ሲፈቀድላቸው ቀዷ ማውጣት ግን አለባቸው አላህም በቁርአኑ((..ከናንተ ውስጥ በሽተኛ ወይንም በጉዞ ላይ የሆነ ሰው ከሌሎች ቀኖች የተወሰነውን መፆም አለበት...)) አል በቀራህ – 184 ሕመምተኛ ሆኖ ጤናው ሁለተኛ የማይፈወስ ከሆነ በየቀኑ ምስኪን ያበላል እንጂ ቀዷ የለበትም::
2. በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ያለች ሴት መፆም ስትከለከል ቀዷ ማውጣት ግን ግዴታዋ ነው:: ዓኢሻ (ረዲየሏሁ አንሃ) (የምን ቀዷ እንድናወጣ ስንታዘዝ ሰላትን ግን አንታዘዝም ነበር) ብለዋል :: ቡኻሪና ሙስሊም
3. እድሜያቸው የገፉ ሽማግሌዎችና አረጋዊያን መፆም የማይችሉ ከሆነ በየቀኑ ምስኪን ማብላት ሲኖርባቸው ቀዷ ግን የለባቸውም::
4. እርጉዝ ወይንም የሚያጠቡ ሴቶች ለራሳቸው ወይንም ለፅንሱ የሚሰጉ ከሆነ ማፍጠር ሲችሉ በየቀኑ ምስኪን ማብላት አለባቸው:: (ኢብኑ ዓባስ ለአንዲት ሴት (አንቺ ፆም የማይችሉት ውስጥ ስለምትጠቃለይ መክፈል እንጂ ቀዷ የለብሽም) ብለዋታል:: ዳረ ቁጥኒ እንዳወሩት
(ሼኽ ዑሰይሚን እርጉዝ ሴት በረመዳን ካፈጠረች ቀዳ ማውጣቲ የተመረጠ ነው ይላሉ::)

ፆም የሚያፈርሱ ነጥቦች

ፆም የሚያፈርሱ ነጥቦች በሁለት ይከፈላሉ

(ሀ) - ፆም የሚያፈርሱና ቀዷ ብቻ ያላቸው

1. እያወቁ ከበሉና ከጠጡ ወይንም ሐራም የሆነውን ሲጋራ ካጨሱ ከቀዷ ጋር ወድያውኑ ተውበት ያስፈልገዋል::
2. እያወቁ ማስታወክ በተመለከተ :- ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ያስታወክ ቀዷ አለበት) ብለዋል:: ሐከም እንዳወሩት

3. የወር አበባና የወሊድ ደም የመጣባት ሴት ጸሐይ ከመጥለቂ በፊት ሊመሽ አካባቢ ቢሆንም እንኳን ፆሟ ይበላሻል::

(ለ) ፆም የሚያበላሽ ቀዷና ከፋራ የሚያስፈልገው :- በረመዳን በቀን የግብረ - ሥጋ ግንኙነት ሲፈፀም ሲሆን አብዛኛዎቹ (ጁምሁር) ከዚህ ሌላ የለም ይላሉ ማካካሻውም (ከፋራው) አገልጋይ ባርያን ነፃ ማውጣት ፣ የማይችል ከሆነ ሁለት ወሮችን አከታትሎ ያለማቂረጥ መፆም ፣ የማይችል ከሆነ ስልሳ ምስኪን ማብላት ሲሆን (አንዳንዶች ቅደም ተከተሉን ማዛባት ቅድመ ሁኔታው (ሸርጥ) አይደለም ይላሉ::

ፆም የማያፈርሱ ነገሮች

1 እረስቶ ፣ ተሳስቶ ፣ ወይንም ተገዶ መብላትና መጠጣት ፆምን አያበላሽም ቀዷም ሆነ ከፋራ አያስፈልጋቸውም:: (ሀ) ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ፆመኛ ሆኖ በመርሳት የበላና የጠጣ ፆሙን ይጨርስ ምክንያቱም አላህ ነው ያበላውና ያጠጣው) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት .
(ለ) (አላህ በሕዝቦቼ ላይ የተሳሳቱትን የረሱትንና የተገደዱበትን ነገር አንስቶላቸዋል (አይጠይቃቸውም) ብለዋል:: ጠብራኒ እንዳወሩት

2 ያለውዱታ ማስታወክ ፆምን አያበላሽም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ፆመኛ ሆኖ ያለፍላጎቱ ያስታወከ ቀዷ የለበትም) ብለዋል:: ሐከም እንዳወሩት

3 ሽማግሌም ሆነ ወጣት ያለስሜት ሚስቶቻቸውን ቢስሙ ፆማቸው አይበላሽም : (ዓኢሻ ረዲየላሁ አንሃ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ፆመኛ ሆነው ይስሙም ይባሽሩም ነበር ነገር ግን ከሁላችሁም የበለጠ ይቆጣጠሩ ነበር) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት

4 በቀን በእንቅልፍ ላይ ሆኖ የዘር ፈሳሽ (መንይ) ከብልት ቢወጣ ፆምን አያበላሽም::

5 ፆመኛ ሆኖ በማሰብ ብቻ ሳያውቅ ወይንም ያለፍላጎት የዘር ፈሳሽ ከብልት ቢወጣ (እንቅልፍ ላይ ባይሆንም) ፆምን አያበላሽም ::

6 ከግብረ ሥጋ - ግንኙነት (ከጀናባ) በኋላ ወይንም ከወር አበባና ከወሊድ ደም ከጠሩ በኋላ ሳይታጠቡ የፈጅር ወቅት ቢገባ ፆምን መቀጠል ይቻላል ዋናው ግዴታ የፈጅር ወቅት ሳይወጣ ተጣድፎ ለሰላት መታጠብ ነው::

7 ውሃ ወደ ጉሮሮ እንዳይገባ ተጠንቅቆ መጉመጥመጥም ሆነ ወደ አፍንጫ መሳብ ፆምን አያበላሽም ይኸውም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለሰሃባው ቀይጥ ቢን ሰብራ (ረዲየሏሁ አንሁ) (ውዱን አስተካክል ከጣቶችህ መሐል ዘርዘር አድርገህ እሽ ፆመኛ ካልሆንክ ወደ አፍንጫህ ውሃ በደንብ ስበህ አስገባ) ብለውታል:: (አህለል ሱነን) (ከዚህ የምንረዳው ፆመኛ በመጠኑም ቢሆን በውዱእ ጊዜ ውሃ ወደ አፍንጫው መሳብ እንደሚፈቀድ ነው::)

8 ፆመኛ በቀን በሁሉም ወቅት ጥርሱን በመፋቂያ እንጨት ወይንም ቡሩሽ በጥርስ ማፅጃ ቡኮ (ኮልጌት) እያጣቀሰ መፋቅ ሲችል ወደ ጉሮሮ እንዳይገባ መጠንቀቅ አለበት::

9 ፆመኛ በቀን ወደ ጉሮሮው እንዳይገባ በመንጠንቀቅ ምግብ መቅመስ ይችላል::

10 ጣዕሙ በጉሮሮ ላይ ቢታወቅም ኩል ፣ የአይንና የጆሮ ጠብታን መጠቀም ይቻላል::

11 ምግብነት የሌለው ከሆነ ማንኛውንም አይነት መድሃኒት በመርፌ መውሰድ ይቻላል::

12 ምራቅ ፣ መቆጣጠር የማይቻል አክታ ፣ ጥቃቅን ብናኞች መዋጥ ፆምን አያበላሽም::

13 ወደ ሆድ የማይገቡ መድኃኒቶች እንደመታሻ ቅባት ፣ ኩል ፣ የአስም መድኃኒት ሚነፋ (ስፕሬይ) የመሳሰሉትን መጠቀም ፆም አያበላሽም::

14 ጥርስን ማስነቀል ወይንም ከአፍ ፣ ከአፍንጫም ሆነ ከማንኛውም የሰውነት ክፍል ደም ቢወጣ ፆምን አያበላሽም::

15 ሰውነትን ለማቀዝቀዝ ጥምን ለመቀነስም ሆነ ለሌላ ጥቅም ገላን መታጠብ ፆምን አያበላሽም::

16 ያመኛ በቀን እጣን ቢያጨስ ፣ ቅባትም ሆነ ሽቶ ቢጠቀም ያምን አያበላሽም ::

17 የፈጅር ሰላት አዛን ሲል በእጅ የያዙትን ምግብ ወይንም መጠጥ እየጎረሱ ወይንም እየጠጡ ከሆነ በእጅ የያዙትን መጨረስ ይፈቀዳል:: ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (አንዳችሁ አዛን ሲሰማ በእጁ ላይ አንዳች ነገር ካለ ሳይጨርሰው እንዳይመልሰው) ብለዋል:: አቡዳውድ

18 ዋግምት ያምን አያበላሽም ምክንያቱም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ያመኛ ሆነው ዋግምት አድርገዋል:: በእርግጥ የኢማም አህመድ (ዋግምት አድራጊውም ተደራጊውም አፈጠሩ) የሚለው ሐዲስ ትክክለኛ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ነገር ግን ለመሻሩ የመጀመርያው ሐዲስም ሆነ ሌሎች በቂ መረጃዎች አሉ:: ኢብኑ ሐዝም እንዳሉት (ዋግምት አድራጊውም ተደራጊውም አፈጠሩ) የሚለው ሐዲስ ትክክለኛነቱ ጥርጥር የለውም ነገር ግን የአቢ ሰዒድን ሐዲስ እንዳገኘ ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለያመኛ ዋግምት ፈቅደዋል ምንግዜም ቢሆን ከትዕዛዝ በኋላ ፍቃድ ከመጣ የመጀመርያው ትዕዛዝ መሻሩን ያመለክታል ስለዚህ ዋግምት አድራጊውም ሆነ ተደራጊው ያማቸው አይበላሽም::) ፈትሑልባሪ 4 / 178

የውዴታ ያሞችና ጥቅማቸው

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የሚከተሉትን ቀኖች ግዴታ ያልሆኑትን ያሞች ለመያም ፍላጎት ነበራቸው::

1 ስድስት ቀኖች በሸዋል ወር መያም:- ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳሉት .

(ሀ) (የረመዳንን ወር ያሞ በሸዋል ወር ላይ ስድስት ቀን ያስከተለ አመት እንደያመ ነው የሚቆጠረው) ብለዋል:: ሙስሊምና ሌሎችም እንደዘገቡት .

(ለ) የረመዳን ወር ያም (ምንዳው እንደ) አሥር ወር ሲታሰብ በሚቀጥለው የሸዋል ስድስት ቀን እንደ ሁለት ወር ታስቦ በጠቅላላው አመት ይሆናል) ብለዋል:: አህመድ እንደዘገቡት

2 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የዓረፋን ቀን መፆም ከዓረፋ በፊት ያለውን ዓመትና ከዓረፋ በኋላ ያለውን ዓመት ወንጀል በአላህ ዘንድ ያስምራል ተብሎ ይታሰባል) ብለዋል

3 የዓሹራን ቀንና ከዓሹራ በፊት ያለውን ቀን መፆም :- (ሀ) ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የዓሹራን ቀን መፆም አላህ ዘንድ ከዓሹራ በፊት ያለውን አመት ወንጀል ያስምራል ተብሎ ይታሰባል) ብለዋል:: ሙስሊም (ለ) (እስከመጪው አመት ከቆየሁኝ ዘጠነኛውንም ቀን እፆመዋለሁ) ብለዋል::

4 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በሻዕባን ወር ላይ ፆም ያበዙ ነበር::

5 ከረመዳን ቀጥሎ የተመረጡት ፆሞች የአላህ ወር በሚባለው ሙሐረም ላይ ነው:: ሙስሊም

6 ሠኞና ሐሙስ ስለመፆም:- .
(ሀ) ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ሰኞና ሐሙስ ሥራዎች አላህ ዘንድ የሚቀርቡበት ቀን ስለሆነ ሥራዬ ፆመኛ ሆኜ እንዲቀርብ እወዳለሁ) ብለዋል:: ነሳኢ እንዳወሩት:: ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ስለሰኞ ቀን ፆማቸው ተጠይቀው ሲመልሱ (ይህ ቀን የተወለደወኩበትና የተወረደልኝ ቀን ነው) አሉ:: ሙስሊም (የተወረደልኝ ማለታቸው ከሰማይ መልዕክት (ወሕይ) የመጣልኝ ቀን ማለታቸው ነው::

7 አያመል በይድ የሚባሉ ሦስት ቀኖችን በየወሩ መፆም :- አንድ ሰሐባ እንደተናገረው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (በየወሩ ሦስት ቀኖች (ማለትም በሂጅሪያ አቆጣጠር ወር በገባ) በአሥራ ሦስተኛው ፣ በአሥራ አራተኛውና ፣ በአሥራ አምስተኛው ቀኖች እንድንፆም ያዙን ነበር) ብሏል:: ነሣኢና ሌሎችም እንደዘገቡት

8 አንድ ቀን እየፆሙ አንድ ቀን ማፍጠር :- ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (አላህ ዘንድ የተወደደው ፆም የዳውድ ፆም ነው አላህ ዘንድ የተወደደው ሰላት የዳውድ ሰላት ነው የሌሊቱን ግማሽ ተኝቶ የሌሊቱን ሲሶ ይቆማል እንደገና የሲሶውን ግማሽ (የሌሊቱን አንድ ስድስተኛ)

ይተኛል በተጨማሪ አንድ ቀን እየፆመ አንድ ቀን ያፈጥር ነበር) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም

ጥብቅ ማሳሰብያ

1 አንዲት ሴት ግዴታ ያልሆኑ የውዴታ ፆሞችን ባሏ አጠገቧ ካለ ያለፈቃዱ መፆም የለባትም ምናልባት ብትፆም እንኳን ባሏ እንድታፈጥር ቢያዛት ማፍጠር ግዴታዋ ነው:: ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ሴት ባሏ አጠገቧ እያለ ያለፈቃዱ መፆም የለባትም ረመዳን ብቻ ሲቀር) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም

2 ፈርድ ያልሆኑ የውዴታ ፆሞችን ነይቶ የሚፆም ሰው ከፈለገ እኩለ ቀን ላይ ሃሳቡን ቀይሮ ማፍጠር ይችላል በተጨማሪ የፈርድ ፆሞችን ካልሆነ በስተቀር የውዴታ ፆሞችን በሌሊት ሳይነይቱ ፈጅር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ምግብም ሆነ መጠጥ ካልቀመሰ በፈለጉበት ሰዓት ፆም መያዝ ይቻላል:: ዓኢሻ (ረዲየሏሁ አንሃ) እንዳወሩት (አንድ ቀን ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ወደ አለሁበት ገብተው (የሆነ ነገር አላችሁ) አሉን ምንም የለንም አልናቸው (እንግዲያውስ ፆመኛ ነኝ) አሉ በሌላ ግዜ በድጋሚ ሲመጡ ሐይስ (የሚባል ምግብ) ሐድያ መጣልን አልኳቸው አሳይኝ ብለው ሲያዩት ፆመኛ ነበርኩኝኮ ብለው በሉ::

የረመዳን ሌሊት ስላት (ቂያም)

1 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የረመዳንን ወር በፍፁም እምነት (በኢማን) ከአላህ ምንዳ አገኛለሁ ብሎ (በኢሕቲሳብ) ሌሊቱን (በሰላት) የቆመ : ያሳለፈው ወንጀሉ ይማርለታል) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም

2 አንድ ሰው ቁዳእ (ከሚባል ስፍራ) ወደ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ዘንድ መጥቶ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ (ላኢላሃ ኢለላህ ብዬ እርሶም የአላህ መልዕክተኛ መሆኖትን እመሰክራለሁ ፣ የአምስት ወቅት ሰላቶችንም እሰግዳለሁ ፣ ወሩንም ፆሜ ረመዳንንም ቆሚያለሁ ፣

ዘካትም ሰጥቻለሁ ታድያ (ይህንን ሥራ) እንዴት ያዩታል? አላቸው እሳቸውም (በዚህ አይነት ሁኔታ የሞተ ከፍፁም አማኞች (ሲዲቂን) ከሰማዕታት (ሹሃዳዎች) ጋርነው) አሉ።። .
ኢብኑ ኹዜማ እንዳስተላለፉት

3 ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በሌሊት አሥራ ሦስት ረከዓት ይሰግዱ ነበር ከነሱም ውስጥ ዊትር እና የፈጅር ረከዓት ይገኙበታል :: ቡኻሪ እንደዘገበው

4 በሌላ ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በረመዳንም ሆነ ከረመዳን ውጪ (የሌሊትን ሰላት) ከአስራ አንድ ረከዓት አስበልጠው አያውቁም :: አሰጋገዳቸውም መጀመርያ አራት ረከዓት ይሰግዳሉ የሰላታቸው ማማርና መርዘም ጥያቄ አያስፈልገውም በድጋሚ አራት ረከዓት ይሰግዳሉ የሰላታቸው ማማርና መርዘም ጥያቄ አያስፈልገውም በመጨረሻ ሦስት ረከዓት ይሰግዳሉ።። ቡኻሪና ሙስሊም (የተራዊህ ሰላት በሌሊቱ መጀመርያ መስገድ ሲቻል በሌሊቱ መጨረሻ መስገድ የተመረጠ ነው።።

ለይለቱል ቀድርና ትሩፋቱ

1. ስለለይለቱል ቀድር ከቁርአን፡- ትርጉም ((እኛ (ቁርአኑን) በመወሳኝቱ (በተከበረችው) ሌሊት አወረድነው ፣ መወሰኛይቱ ሌሊት ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ ፣ መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺሕ ወር በላጭ ናት ፣ በርሷ ውስጥ መላእክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ ፣ እርሷ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም ብቻ ናት።)) አል ቀድር 1 - 5
2. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በረመዳን የመጨረሻዎቹ አሥር ቀኖች (ዓሸረል አዋኺር) ሲገባ ወገባቸውን ያጠብቃሉ ፣ ሌሊቱን አይተኙም ቤተሰባቸውንም ይቀሰቅሳሉ።። ቡኻሪና ሙስሊም (ወገባቸውን ያጠብቃሉ ማለት ለዒባዳ ታጥቀው ይነሳሉ ሴቶቻቸውንም ይርቃሉ ማለት ነው)

3. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ለይለቱል ቀድርን በፍፁም እምነት (በኢማን) ምንዳ አገኝበታለሁ ብሎ (በኢሕቲሳብ) (በሰላት) የቆመ ያለፈው ወንጀሉ ይታበስለታል) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም
4. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ለይለቱል ቀድርን በዓሸረል አዋኺር ዊትር ቀኖች ተጠባበቁ) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም
(የዊትር ቀኖች ማለት 21 - 23 - 25 - 27 - 29 ናቸው)
5. ዓኢሻ (ረዲየሏሁ አንሃ) እንዳሉት ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የአላህ መልክተኛ ሆይ የለይለቱል ቀድር ሌሊት መሆኑን ካወቅኩኝ ምን ልበል?) አልኳቸው :: እሳቸውም (አላሁመ ኢነከ ዓፍው ቱሒቡል ዐፍወ ፈዕፉ ዓኒ) ትርጉም (አላህ ሆይ አንተ መሐሪ ነህ ምህረት ማድረግም ትወዳለህ ማረኝ) በይ አሉኝ :: ተርሙዚ እንደዘገቡት

ኢዕቲካፍ

1. በሸሪዓው ኢዕቲካፍ ማለት :- ወደ አላህ ለመቃረብ ነይቶ ለተወሰነ ጊዜ (ቀን) መስጊድ ውስጥ መቀመጥ ማለት ነው::
2. ኢዕቲካፍ በሸሪዓው የተፈቀደ ለመሆኑ ሁሉም ዓሊሞች ይስማሙበታል : ይኸውም ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በረመዳን የመጨረሻ አሥር ቀኖች (ዓሸረል አዋኺር ላይ እስከሚሞቱበት ጊዜ ድረስ ኢዕቲካፍ ያደርጉ ነበር ከሳቸውም በኋላ ባለቤቶቻቸው ኢዕቲካፍ ያደርጉ ነበር:: ቡኻሪና ሙስሊም የተስማሙበት
3. ኢዕቲካፍ በሁለት ይከፈላል .
(ሀ) ኢዕቲካፍ ዋጂብ (የግዴታ ኢዕቲካፍ :- ይህም አንድ ሰው ስለት (ነዝር) አድረጎ በራሱ ላይ የሚጭነው የግዴታ ኢዕቲካፍ ነው:: .
(ለ) ሁለተኛው ሱና የሆነው ኢዕቲካፍ ሲሆን ይኸውም ሙስሊም በረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በመመራት ወደ አላህ ለመቃረብ ብሎ በውዴታ በተለይ በረመዳን

የመጨረሻ አሥር ቀኖች ውስጥ ወደ መስጊድ ለተወሰነ ቀን ጠቅልሎ መግባት ማለት ነው።።

4. ወደ ኢዕቲካፍ የሚገባበት ወቅት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የፈጅር ሰላት ከሰገዱ በኋላ (በጠዋት) ለኢዕቲካፍ ወደ መስጊድ ይገቡ ነበር ።። ቡኻሪና ሙስሊም የተስማሙበት ሐዲስ (ጠዋት ማለት በረመዳን 20 - ነው) ሌላው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በሸዋል የመጨረሻ አሥር ቀኖች ኢዕቲካፍ አድርገዋል።። ቡኻሪና ሙስሊም የተስማሙበት ሐዲስ
5. የኢዕቲካፍ ቅድመ ሁኔታዎች (ሹሩጥ) ፡-ኢዕቲካፍ የሚያደርግ ነፍስ ያወቀ ፣ ንፅህናውን የጠበቀና ከጀናባ የጠራ መሆን አለበት ሴቶችም ከወር አበባና ከወሊድ ደም የጠሩ መሆን አለባቸው ።።
6. የኢዕቲካፍ መሠረቶች (አርካን) ፡- መስጊድ ውስጥ ፣ ወደ አላህ ለመቃረብ ነይቶ ፣ ተረጋግቶ መቀመጥ ፡ ናቸው።።
7. ኢዕቲካፍ ላደረጉ ሰዎች የሚፈቀዱ ነጥቦች፡-
(ሀ) ኢዕቲካፍ ያደረገ ሰው ለቤተሰቡ ጉዳይ ከመስጊድ መውጣት ይችላል።።
(ለ) ኢዕቲካፍ ያደረገ ሰው ፀጉሩን ማበጠርና መላጨት ፣ ጥፍሮቹን መቁረጥ ፣ ሰውነቱን ማፅዳት ፣ የተሻለ ልብሶቹን ለብሶ መቀባባት ይችላል።።
(ሐ) ግዴታ ለሆኑ ጉዳዮች ለምሳሌ ውዱእ ለማድረግ ፣ ሽንትቤት ለመጠቀም ፣ የሚያቀርብለት ከሌለ ምግብና መጠጥ ፍለጋ እና ለመሳሰሉት ጉዳይ ከመስጊድ መውጣት ሲቻል (ጉዳዩን እንደጨረሰ መመለስ ግዴታው ነው።።)
(መ) ኢዕቲካፍ ያደረገ ሰው መስጊድ ውስጥ በጥንቃቄ ንፅህና ጠብቆ መብላት ፣ መጠጣትና መተኛት ይችላል።።
8. የኢዕቲካፍ ሥርዓት ፡- ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) እንዳሉት (ኢዕቲካፍ የሚያደርግ ሰው ሱናው ግዴታ ላልሆነ ነገር ከመስጊድ ያለመውጣት ፣ የታመመን እንኳን መጠየቅ የለበትም ፣ ሚስቱን በስሜት መነካካትም ሆነ መገናኘት ክልክል ነው ፣ ከመስጊድ ውጪ ኢዕቲካፍ ማድረግም

አይፈቀድም ፣ ኢዕቲካፍ ሲያደርግ መፆሙ ሱና ነው።) በይሃቂ እንደዘገቡት

9. ኢዕቲካፍ የሚያበላሹ :- የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም ፣ እያወቁ ያለምክንያት ከመስጊድ መውጣት ፣ በጤና መታወክ አፅምሮን መሳት ፣ ሴቶች በወር አበባና በወሊድ ደም ምክንያት : ከላይ የተዘረዘሩት ባጠቃላይ ኢዕቲካፍን ያበላሻሉ።
10. ኢዕቲካፍ ለሚያደርጉ የሚወደድ ሥራ :- ግዴታ ያልሆኑ ትርፍ ዒባዳዎችን ማብዛት ይኸውም ሱና ሰላት ፤ ቁርአን መቅራት ፣ ዚክር ማብዛትና የዲን ኪታቦችን መቅራት የመሳሰሉት ናቸው።
11. ኢዕቲካፍ ላደረገ ሰው የሚጠላው፡- በንግግርም ሆነ በተግባር ጊዜውን በማይረባ ነገር ማሳለፍ ፣ ወደ አላህ የሚያቃርበው መስሎት ፈፅሞ አልናገርም ማለት የመሳሰሉት የተጠሉ ናቸው።
12. የኢዕቲካፍ ጥቅም:- ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ኢዕቲካፍ ከወንጀል ያርቃል ምንዳውም ከፍተኛውን የሐሰናት ደረጃ ያስገኛል) ብለዋል። ኢብኑ ማጃህ እንዳስተላለፉት

ዘካተል ፊጥር

1 ብያኔው፡- ሙስሊም በሆኑ ግለሰቦች በሕፃን ፣ በሽማግሌ ፣ በወንድ በሴት ፣ ነፃ በሆነ ወይንም አገልጋይ (ባርያ) በሆነ ላይ በጠቅላላ የነፍስ ወከፍ ግዴታ ነው።

2 ዘካተል ፊጥር ማውጣት የሚገባው :- ነፃ የሆነ ሙስሊም፡ ለራሱና ለቤተሰቡ ከአንድ ቀንና ሌሊት ቀለብ ተርፎት 2.5 ኪግ (ሳዕ) በላይ የሚያህል ጥሬ ያለው ለራሱ ፣ ለባለቤቱ ለልጆቹና በሥሩ ለሚያስተዳድራቸው ማውጣት አለበት ::

3 የዘካተል ፊጥር ልኩ : ቀለቡ (ቁቱ) ከተምር ፣ ከገብስ ወይንም ከዱቄት ሲሆን አብዛኛው አገር አሰፋፈሩ በሩዝ በስንዴ በመሳሰሉት ነው መጠኑም በግምት (ሁለት ተኩል ኪ.ግ) ይሆናል። ኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ አንሁማ) እንዳሉት (ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በረመዳን ዘካተል ፊጥር ነፃም ሆነ አገልጋይ

ባርያ በሆነ በወንድም በሴት ፣ በሕፃንም በአዋቂ ላይ ሳዕ (2.5 ኪ.ግ) የሚያህል መጠን ከተምር ወይንም ከገብስ እንዲወጣ አዘዋል።) ቡኻሪና ሙስሊም

4 ዘካተል ፊጥር የታዘዘበት ጥበቡ፡-
(ሀ) ፆመኛ በሚያምበት ጊዜ በቃልም ሆነ በተግባር የተሳሳታቸውን ጥፋቶች ያፀዳለታል።
(ለ) ድሃዎችና ምስኪኖች የዒድ ቀን በሚያገኙት ዘካተል ፊጥር ሰው ከመለመን ይቆጠባሉ።

5 አወጣጡ በሐዲስ እንደተገለፀው ለምስኪን መሆን አለበት ይኸውም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ዘካተል ፊጥር ፆመኛ የፈፀመውን መጥፎ ቃልና ተግባር ሲያፀዳ ምስኪንን ይመግባል) ብለዋል።

6 ዘካተል ፊጥር የሚወጣበት ወቅት የግዴታ ከዒድ ሰላት በፊት መሆን አለበት ወይንም ከዒድ ቀን በፊት አንድ ቀን ወይንም ሁለት ቀን አስቀድሞ ማውጣት ይቻላል። ኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ አንሁማ) እንዳሉት (ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ዘካተል ፊጥር ፆመኛ የፈፀመውን መጥፎ ቃልና ተግባር ሲያፀዳ ምስኪንን ይመግባል ከዒድ ሰላት በፊት የሰጠ ተቀባይነት ያለው ዘካ ይሆንለታል ከሰላት በኋላ የሰጠ ከሰደቃዎች እንደማንኛውም ሰደቃ ነው የሚቆጠረው) ብለዋል ።
አቡ ዳውድና ኢብኑ ማጃህ እንዳስተላለፉት

የሁለቱ ዒዶች ሰላት

1. የዒድ ቀን ተጣጥበህ ተቀባብተህ ከልብሶችህ የተሸለውን ለብሰህ ቤተሰብህን ልጆችህን በማስከተል ወደ ዒድ ሰላት መስገጃ መሄድ ፡ ስትመለስ የሄድክበትን መንገድ መቀየር ሱና ነው።
2. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የዒድ አል ፊጥር ቀን በጠዋት ቁጥሩ ዊትር በሆነ ተምር ሳያፈጥሩ አይወጡም ነበር። ቁጥሩ ዊትር ማለት ብዛቱ ሙሉ ያልሆነ 1 - 3 - 5 - 7 - 9 ማለት ነው።
3. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የሁለቱ ዒዶች ቀን በወር አበባ ላይ እያለን ወደ ዒድ ሰላት መስገጃ ቦታ እንድንወጣ

ያዙን ነበር በወር አበባ ላይ ያለች ሴት ሰላት ሳትሰግድ ለሙስሊሞች የሚደረገውን መልካም ኢስላማዊ ጥሪ ትከታተላለች:: ጠያቂዋ ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ከኛ መሐል አንዷ የምትለብሰው ጂልባብ ከሌላትስ ? ብላ ስትጠይቅ (እህቲ ጂልባቡዋን ታለብሳታለች) አሉ ::

4. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የሁለቱ ዒዶች ቀን ወደ መስገጃ ቦታ ሲደርሱ መጀመርያ በሰላት ነው የሚጀምሩት:: ቡኻሪ እንደዘገበው
5. ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የዒድ አልፊጥር ሰላት በመጀመርያው (ረከዓ) ሰባት ጊዜ ተክቢራ ሲባል በሁለተኛው አምስት ጊዜ ይባላል ከሁለቱም ረከዓቶች ተክቢራዎች በኋላ ይቀራል) ብለዋል :: አቡ ዳውድ እንዳወሩት

ከሐዲሶቹ የሚገኝ ጥቅም

1. የሁለት ዒዶች ሰላት የሚሰገዱት ሁለት ረከዓት ሲሆን በመጀመርያው ረከዓት ሰባት ጊዜ ተክቢራ ሲባል በሁለተኛው ረከዓ አምስት ጊዜ ተክቢራ ይባላል ከተክቢራዎቹ በኋላ እንደተለመደው ፋቲሃ ተቀርቶ ከቁርአን አናቅፅ የገራውን በመቅራት ይሰገዳል::
2. የዒድ ሰላት መስገጃ ቦታ ለስተማ ቅርብ ሆኖ ከመኖርያ ቤቶች ራቅ ብሎ ሜዳ ላይ ሲሆን ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የሁለቱን ዒዶች ሰላት ለመስገድ ከሕፃናት ከሴቶችና ከወጣቶች ጋር ይወጡ ነበር በወር አበባ ላይ ያለች ሴት እንኳን ሳትቀር አብራቸው ትወጣ ነበር:: ሐፍዝ ኢብኑ ሐጀር ፈትሁል ባሪ ላይ እንዳብራሩት የዒድ ሰላት (በዝናብና በብርድ) ሰበብ ግዴታ ካልሆነ በስተቀር መስጊድ ውስጥ መሰገድ የለበትም ይላሉ::
3. የዒድ አልፊጥር ተክቢራ የሚጀመረው ለዒድ አጥቢያ ምሽት (ለይለተል ዒድ) ሲሆን የሚያበቃው የዒድ ሰላት ከተሰገደ በኋላ ነው አላህም በቁርአኑ:- .

{ وَلِتُكْمِلُواْ الْعِدَّةَ وَلِتُكَبِّرُواْ اللّهَ عَلَى مَا هَدَاكُمْ وَلَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ

ትርጉም ((..ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህንን ደነገግላችሁ)) አል በቀራህ - 185

የዒድ ቀን የሚታዩ ፈጠራዎች (ቢድዓ)

1. አንዳንድ ቦታዎች በዒዶች ቀን ቀብርን መዘየር እየተለመደ ነው ይህ ደግሞ በኢስላም ምንም መረጃ የሌለው ፈጠራ ነው::

2.አንዳንድ ቦታ በዒድ ቀን በመቃብሮችና በዒድ ማክበሪያ ቦታዎች ወንድና ሴት ሽሪዓው በማይፈቅደው መልኩ ይቀላቀላሉ : ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ከሴት ጋር በመቀላቀል የሚመጣውን ፈተና ሲያስጠነቅቁ (ከኔ በኋላ ወንዶች በሴቶች ከመፈተን የበለጠ የሚጎዳቸው ፈተና አልተውኩም) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት

3. መቃብሮች አካባቢ ቁርአን መቅራት ፍፁም የተከለከለ ነው ለዚሁም መረጃ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ቤታችሁን መቃብር አታድርጉት (ቁርአን ቅሩበት) የአል በቀራህ ምዕራፍ የሚቀራበት ቤት ሸይጣን ይሸሸዋል) ብለዋል:: ሐከም እንዳስተላለፉት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለሰሐቦቻቸው ወደ መቃብር ሲሄዱ የሚከተለውን ዱዓ ያስተምሯቸው ነበር:- (አሰላም ዓለይኩም አህለ ዲያር ሚነል ሙእሚኒን ወል ሙስሊሚን አስአለላሁ ለና ወለኩም ዓፍያ) ትርጉም (አሰላም ዓለይኩም ከሙስሊሞችና ከሙእሚኖች ወገን የሆናችሁ የቀብር ባለቤቶች አላህ የፈለገ ጊዜ እኛም እንከተላችኋለን ለኛም ሆነ ለናንተ ሰላሙን ከአላህ እንጠይቃለን) ማለት ነው ::

ተቀባይነት ያላቸው ዱዓዎች

الدعاء المستجاب

١ـ قال رسول الله ﷺ: (ماأصاب عبداً همٌّ ولاحزَن فقال:

اللهم إني عبدك، وابنُ عبدك وابنُ أمَتك، ناصيتي بيدك، ماضٍ فيّ حكمُك، عَدلٌ فيَّ قضاؤك، أسألك بكل اسم هُوَ لك، سمَّيت به نفسَك، أو أنزلته في كتابك، أو علَّمته أحدًا مِن خلقك، أو استأثرتَ به في عِلم الغيب عندك أن تجعل القرآن ربيع قلبي، ونور بصري، وجلاء حزني، وذهاب هَمِّي وغَمِّي: إلا أذهب الله همَّه وحزنَه، وأبدلَه مكانَه فرحا). «صحيح رواه أحمد»

٢ـ وقال ﷺ: (دعوة ذي النون إذ دعا بها وهو في بطن الحوت:

﴿لَّآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنتَ سُبْحَٰنَكَ إِنِّي كُنتُ مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٨٧﴾﴾

لم يدعُ بها رجلٌ مسلمٌ في شيءٍ قط إلَّا استجاب الله له) «صحيح»

٣ـ كان رسول الله ﷺ إذا نزل به هَمٌّ أو غَمٌّ قال:

(يا حَيُّ يا قيوم برحمتك أستغيث) «حسن رواه الترمذي»

٤ـ سمع الرسول ﷺ رجلاً يقول:

اللهم إني أسألك بأني أشهدُ أنك أنتَ الله لا إله إلاَّ أنت الأحدُ الصمَدُ الذي لم يلِدْ ولم يُولَد ولم يَكُنْ له كُفُوًا أحَد:

فقال ﷺ: (والذي نفسي بيده لقد سأل اللهَ باسمه الأعظم الذي إذا دُعِيَ به أجاب وإذا سُئِل به أعطى) «صحيح رواه أحمد»

የፈውስ ዱዓ

دعـــاء الشفـــاء

١ـ (ضَعْ يدك على الذي تألَّمَ من جسدك وقل:
بسم الله ثلاثاً، وقل سبع مرات:
أعوذ بالله وقدرته من شَرِّ ما أجدُ وأُحاذر) «رواه مسلم»

٢ـ (اللهم رَبَّ الناس، أذهب البأس، إشفِ أنت الشافي لا شفاءَ إلا شفاؤك شفاءً لا يُغادرُ سَقماً) «متفق عليه»

٣ـ (أعوذ بكلمات الله التامَّة من كل شيطان وهامَّة ومن كل عين لامَّة) [هامَّة: حشرات سامّة، لامَّة: سوء] «رواه البخاري»

٤ـ (مَن عاد مريضاً لم يحضُر أجلُه فقال عنده سبع مرات:
أسأل الله العظيم، ربَّ العرش العظيم أن يشفيك،
إلا عافاه الله) «صححه الحاكم ووافقه الذهبي»

٥ـ (مَن رأى مُبتلى فقال: الحمد لله الذي عافاني مما ابتلاك به وفضَّلني على كثير ممَّن خلق تفضيلاً
لم يُصِبْه ذلك البلاء) «حسن رواه الترمذي»

٦ـ اقرأ الفاتحة والمعوّذتين واطلُب الشفاء من الله وحده، واجمع بين الدعاء والدواء، وتصدَّق للفقراء لِتُشفى بإذن الله.

٧ـ إستعمل العسل لقوله تعالى: ﴿فِيهِ شِفَآءٌ لِّلنَّاسِ﴾. «النحل: ٦٩»

٨ـ قال رسول الله ﷺ: (أمثل ما تداويتم به الحجامة) «رواه البخاري»

٩ـ وقال رسول الله ﷺ: (في الحبة السوداء، شفاء مِن كل داء، إلا السام). [السام: الموت] «متفق عليه»

የምርጫ ዱዓ

دعـاء الاستخـارة

عن جابر رضي الله عنه قال :

كان رسول الله ﷺ يُعلِّمنا الاستخارة في الأمور كلها كما يُعلِّمنا السورة من القرآن ، يقول :

(إذا همَّ أحدكم بالأمر فليركع ركعتين من غير الفريضة ، ثم ليقل :

اللهم إني أستخيرك بعلمك ، وأستقدرُك بقُدرتك ، وأسألك من فضلك العظيم ، فإنك تقدِرُ ولا أقْدِرُ ، وتعلمُ ولا أعلم ، وأنت علاَّم الغيوب .

اللهم إن كنتَ تعلم أن هذا الأمر خيرٌ لي في ديني ومعاشي وعاقبة أمري ، فاقدُرهُ لي ، ويَسِّرْهُ لي ، ثم بارِكْ لي فيه ، وإن كنتَ تعلَمُ أن هذا الأمر شرٌّ لي في ديني ومعاشي وعاقبة أمري ، فاصرفهُ عني واصرفني عنه ، واقدُرْلي الخيرَحيث كان ثم رضِّني به)(رواه البخاري)

(قال : ويسمي حاجته) [من زواج أو شركة أو سفر أو غيره]

وهذه الصلاة والدعاء يفعلهما الإنسان لنفسه كما يشرب الدواء بنفسه مُوقناً أن ربه الذي استخاره سَيوجِّههُ للخير ، وعلامة الخير تيسُّر أسبابه ، واحذر الاستخارة المبتدعة التي تعتمد على المنامات وحساب اسم الزوجين وغيرهما مما لا أصل له في الدين .

የመንገደኛና የተሳፋሪ ዱዓ

دعاء الركوب والسفر

١ـ إذا ركبت سيارة أو مركوبًا فقل :

(بسم الله والحمد لله، سبحان الذي سخر لنا هذا وما كنا له مقرنين [مطيقين]، وإنا إلى ربنا لمنقلبون [راجعون]، الحمدلله، الحمدلله، الحمد لله، الله أكبر، الله أكبر، الله أكبر، سبحانك إني ظلمتُ نفسي فاغفِرْ لي فإنه لايغفر الذنوب إلاأنت)

«رواه الترمذي وقال: حسن صحيح»

٢ـ قال ﷺ : (من أراد أن يسافر فليقل لمن يَخلِف :

أستودعُكم الله الذي لا تضيعُ ودائعُه)

«حسن رواه أحمد»

٣ـ ويقال للمسافر : (زوَّدك الله التقوى، وغفر ذنبك، ويسَّر لك الخير حيثما كنت)

«رواه الترمذي وحسَّنه وهو كما قال»

٤ـ إذا ركبت وسافرت فقل :

(اللهم إنانسألك في سفرناهذاالبِرَّوالتقوى ومن العمَل ماترضى اللهم هَوِّن علينا سفرنا هذا، واطوِ عنا بُعْدَه.

اللهم أنت الصاحبُ في السفر، والخليفةُ في الأهل.

اللهم إني أعوذ بك من وعَثاء السفر [شدَّته]، وكآبة المنظر وسوء المُنقلَب [الرجوع]في المال والأهل).

«رواه مسلم»

٥ـ وإذا رجع المسافر قالهن وزاد عليهن :

(آيبون تائبون عابدون لربنا حامدون)

«رواه مسلم»